የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሱጁድ ውስጥ እንዲህ ይሉ ነበር "አላሁመግፊርሊ ዘንቢ ኩለሁ ዲቀሁ ወጂለሁ፣ ወአወለሁ ወአኺረሁ፣ ወዐላኒየተሁ ወሲረሁ"» ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ደቂቁንም ትልቁንም፣ የመጀመሪያውንም የመጨረሻውንም፣ ግልፁንም፣ ድብቁንም ወንጀሌን ሁሉንም ማረኝ።

ከአቡ ሁረይራ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሱጁድ ውስጥ እንዲህ ይሉ ነበር "አላሁመግፊርሊ ዘንቢ ኩለሁ ዲቀሁ ወጂለሁ፣ ወአወለሁ ወአኺረሁ፣ ወዐላኒየተሁ ወሲረሁ"» ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ደቂቁንም ትልቁንም፣ የመጀመሪያውንም የመጨረሻውንም፣ ግልፁንም፣ ድብቁንም ወንጀሌን ሁሉንም ማረኝ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) በሱጁዳቸው ወቅት እንዲህ እያሉ ዱዓእ ያደርጉ ነበር: "አላህ ሆይ ወንጀሌን ማረኝ" በመሸሸጊያህ ሸሽገኝ፤ ተከትሎት የሚመጣውን መከራንም ጠብቀኝ፤ ይቅር በለኝ፤ እለፈኝ (ሁሉንም) ማለትም (ደቂቁንም) ትንሹንም ጥቃቅኑንም፤ (ትልቁንም) ግዙፉንም ብዙውንም፤ (የመጀመሪያውንም) የመጀመሪያውን ወንጀሌንም፤ (የመጨረሻውንም) በነርሱ መካከል ያለውን ወንጀሌንም (ግልፁንም ድብቁንም) ከአንተ በቀር ማንም የማያውቀውን ወንጀሌንም ማረኝ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/5470